# በስለት ወልጄህ፣ በስለት ተበላህ?

ልጅ ላገኝ ጓጉቼ፣
ከሌሎች አይቼ፣
ልጅን እንዲሰጠኝ አምላክን ለመንኩት፣
ስጠኝ እሰጥሀለሁ ተሳልኩኝ በማለት፡፡
ከቶ አልገባኝም ሳጨው ለመከራ፣
ትልቁን ተመኘሁ ሆኖ እንዳይቀር ተራ፡፡
በስለት ወልጄህ፣
በስለት ተቀላህ?

አንተን እያበላሁ ለራሴ ተርቤ፣
ሳትጠግብ ከቶ ላልበላ ጠግቤ፣
ብርድ እንዳይነካህ አሙቄህ በእቅፌ፤
ሳስተኛህ እንኳን ደልድዬ አንጥፌ፡፡
ወላጅ ይፍረደኝ፣
እርሱ ይዳኘኝ፡፡

ከእውቀት እንዳይጎድል ሳልማር አስተምሬ፣
ኮትኩቼ አሳድጌ እንዲበቃ ለፍሬ፤
ደልቶኝ አልነበረም በጉድለት ከስሬ፣
ያሳደግሁት ልጄ አንጀቱን አስሬ፤
ሞቱን አልሞትኩለት በእሱ ተቀይሬ፣
ወይኔ ልበል እንጂ ላልቅሰው አምርሬ፡፡
ወላጅ ይፍረደኝ፣
እሱ ይዳኘኝ፡፡

እንዳላስጥለው አንገቱን አቅፌ፣

ሞቱን እንዳልለውጠው ላዩ ተለጥፎ፡፡
አጠገቤ የለ ሄዷል ሀገር ቆርጦ፣
ባእድ ምድር ነው አይደረስ ተሩጦ፡፡
ዋ ልጄ! ዋ ልጄ! እኔን ክንብል ደፋ፣
ከዚህ የሚያድንህ አንድ ወገን ጠፋ?
ማለትህ አይቀርም ወይኔ እናቴ፣
ለእኔም እኮ ነበርክ ጌጤና ስስቴ፤
ላስጥልህ አልቻልኩም በእናትነቴ፡፡
ወላጅ ይፍረደኛ፣
እሱ ይዳኘኛ፡፡

አምጬ የወለድኩት በስለት ሲቀላ፣
ተለብልቦ ነዶ በእሳት ሲበላ፤
እኔስ አቅም አጣሁ አምላክ አንድ በላ፡፡
አይንህን ላላየው ድምጽህን ላልሰማ፣
ድፍት ብለህ ቀረህ ተዋጥክ በጨለማ።
በስለት ወልጄህ፣
በስለት ተበላህ?

ኢትዮጵያውያን እናቶችን ድምፅ በመወከል
ከበቀለች ጥሩዬ   04-23-15